# የሽኩቻው በትር

**በይበልጣል መኮንን**

የአንድ ሀገር ንጉስ በብዙ ጉልበትና ገንዘብ ያሰራውን ወህኒ ቤት የአካባቢውን ማህበረሰብ እና ባለስልጣን ሰብስበው እንዲህ በሚል ንግግር እንዳስመረቁት በማህበረሰብ ዘንድ እስካሁን ድረስ ሲነገር ይኖራል፡፡ “የአባታችን ርስተ-ጉልት የሆነውን ወህኒ ቤት መርቀን ስንከፍትላችሁ፤ እናንተም በተለመደው ባህላችሁ በመተሳሰብ እንድትተሳሰሩበት ነው” በሚለው የምፀት ንግግር ያሰሩትን ወህኒ ቤት በእንዲህ አይነቱ ታሪካዊ ንግግር መርቀው እንደከፈቱት ይነገራል፡፡ ንግግሩ የሀገራችን ነባራዊሁኔታን ጋር የሚመሳስል መስሎ ስለተሰማኝ የሀሳቤ መንደርደሪያ አደረኩት፡፡

በእኛም ሀገር እየሆነ ያለው ይህው ነው፡፡ አሁን ላይ እየተስተዋለ ያለው የሀገራችን የፖለቲካ ፣ የሙስና እና የኢኮኖሚ ሽኩቻዎች መጨረሻቸው የተባለው የንጉሱ ንግግር ነው፡፡ እንደሀገር እየተደረጉ ያሉት ሽኩቻዎች ተጠናክረው በመቀጠላቸው ለገጠመን የኑሮ ውድነት እና ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገት መቀጨጭ ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ ይነገርላቸዋል፡፡ እነዚህ የፖለቲካ ፣ የሙስና እና የኢኮኖሚ ሽኩቻዎች ከሕዝብና ከጋራ ጥቅም ይልቅ በዋናነት ብህሊናቢስ “እኔ ብቻ” በሚል አስተሳሰብ ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ በመሆናቸው በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኝን ሕጋዊና ትክክለኛ የንግድ ተግባሩን አዛብተው የኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር የሚያደርጉ በመሆናቸው የተነሳ ነው፡፡

እንደነዚህ አይነት የስግብግብነትና የእኔ ብቻ የሚል ግላዊ ፍላጎት ላይ ያነጣጠሩ ሽኩቻዎች ሕጋዊና ትክክለኛ የንግድ ሰንሰለት ህጋዊነቱን ጠብቆ እንዳይፈፀም የሚያግዱ እጅግ አደገኛ አካሄድን የተላበሱ ሲሆኑ ሰዎች በትጋት ሰርተው ሀብታቸውን እንዳያዳብሩ፣ ቤታቸውን እንዳያቃኑ፣ ሀገራቸውን እንዳይገነቡ እና ኑሯቸውን እንዳይደግፉ የሚያደርጉ መሆናቸው ነው፡፡ እየተከናወነ ያለው የእኔ ብቻ ሽኩቻ ውሎ ሲያድር በህብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስር ላይ የሚያስከትለው የስነ-ልቦና ጉዳት  እንደዚሁ አደገኛ ነው፡፡ ባልተገባ መንገድ በሚደረጉ ሽኩቻዎች ምክንያት በየቀኑ እየጨመረ የሚሄደውም የሸቀጦች ዋጋ መናር በዜጋው ላይ ክፉኛ በትሩን አሳርፎ ህዝቡን ለምሬት እየዳረገ መጥቷል፡፡ በዚህ ልክ የችግሩን አሳሳቢነት ተረድቶ የመፍትሔ ሀሳብ ከማፈላለግ ይልቅ በመገፋፋት እሳቤ ችግሩ መፍትሄ አጥቶ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

ሌላው ጉዳይ እንደዚህ አይነት የፖለቲካው ፣ የሙስናው እና የኢኮኖሚው ሽኩቻዎች ተሳሳሪነታቸውም ሆነ ተባባሪነታቸው አንድ ጉዳይ ላይ ያነጣጠሩ መሆናቸው ነው፡፡ ሽኩቻዎቹ የስነ- ምግባር መርሆዎችን ጥሰው ህሊና ቢስ በሆነ አስተሳሰብ የመንግስትን ተቋማት መነገጃና መማለጃ የማድረግን አስተሳሰብ የተላበሱ መሆናቸው ነው፡፡ አደገኛ አካሄዳቸው የህዝብን ሀብት የግል ከማድረግ ባለፈ የሀገርን ሀብት ወደ ውጭ ሀገር እስከ ማሸሽ ድረስ የተላበሰ እኩይ እሳቤን የተላበሱ ናቸው፡፡ ይህ እኩይ የስነ-ልቦና ለውጥ እያደር አካሄዱን አጠናክሮ ቀጥሎ ጉቦ መጠየቅ እና መስጠት አፀያፊ ስነ-ምግባር መሆኑ ቀርቶ ህጋዊ ተግባራቸው ሆኗል፡፡

“ታማኝ ነው ያሉት የስለት እቃ ይሰርቃል” እንደሚባለው ሁሉ የተሰጣቸውን ስልጣን ተገን አድርገው የግል ወይም የድርጅት ኢኮኖሚያዊ ቋታቸውን መሙላት የተለመደ ተግባራቸው ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ በተለይም ደግሞ እንደዚህ አይነት አባዜ ያለባቸው ግለሰቦች ወደ ስልጣን ሲመጡ ስለ ዲሞክራሲያዊ ልዕልና ፣ ስለ ህዝባዊ ፍትህ ፣ ስለ ሕዝብ እድገት ፣ በህዝብ ሀብት ስለበለጸጉ የቀድሞ ባለስልጣናት ማውጋት እና ሙስና በሀገር ላይ ስለአደረሰው ዘርፈ ብዙ ችግር በሚዲያ ብቅ እያሉ ማውራት የሽፋን ልብሳቸው ነው፡፡ ዳሩ ግን አንድ ጀምበር ሳይሻገሩ ሙስናው የግላቸው ፣ ፍትሁም በአድልኦ የተሞላ ፣ ሰላሙም እንደዚሁ ጦር የሚሰብኩበት የግል በትራቸው አድርገው ድብቅ እና የመጨረሻ ዓላማቸውን በዳሀው ሕዝብ ጫንቃ ላይ ግለሰባዊ ፍላጎታቸውን ማርካት ህልማቸው ነው፡፡

በዚህ መልኩ ባጠመዱት እኩይ ሴራ የኢኮኖሚያዊ-ዕዙን ወደ ባለስልጣናዊ የኢኮኖሚ- ዕዝ ስርዓት ቀይረው ሕዝብን ለድህነት ሀገርን ለኃላቀርነት ዳርገው የተንጣለለ የሀብት ማማ ላይ መውጣት ግባቸው ቢሆንም የመጨረሻ ማረፊያቸው የተባለው ወህኒ ቤት ነው። የአባት ምርቃት ሆኖም ይሁን የሀበሻ የአጥንትና የደም ትስስር ባይታወቅም "በመተሳሰብ መተሳሰር" የተለመደ ባህላችን ማሳያ ሆኖ ይህው አሁን ድረስ ዘልቆ የትውልዱ እኩይ የውርስ ተግባር ፍሬ አፍርቶ ማየት ችለናል። የማታ ማታ ቢሆንም ድብቅ ገመናቸው ተጋልጦ ወደ ዘብጥያ መውረድ ፀሀይ የሞቀው ሀገር ያወቀው ፍፃሚያቸው መሆኑ ግልፅ ነው።

አሁን ላይ ዜጎች ከዛሬ ነገ አገራችን ከድህነት ወጥታ፣ ተለውጣና አድጋ ኑሯችን ይሻሻላል በሚል የጣሉት ተስፋ በፖለቲካ ፣ በሙስናና በኢኮኖሚ ሸኩቻ ተውጦ በምተኩ የኑሮ ውድነቱ እንዲነግስ ተደርጓል፡፡ የሸኩቻዎቹ መብዛትና መባባስ ምክንያት የኑሮ ውድነቱ ገዝፎ የሸቀጥ ዋጋ እጅግ ንሯል፡፡ በተለይም ደግሞ በንግድ ሰንሰለቱ ውስጥ የሚስተዋሉት ሸኩቻዎች የግብይት ትስስሩ እጅግ እንዲራዘም የሚያደርጉ ሲሆኑ ገበያው ላይ ጤናማ ውድድርን አጥፍተው የዋጋ ውድነት እንዲፈጠር የሚያካሂዱት አሻጥር አደገኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህ ጉዳይ በገበያው ላይ አለመረጋጋትንና የዋጋ ግሽበትን ማስከተሉ ለየት የሚያደርገው ነው

የችግሩ ግዝፈት ሚዛናዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ ዕድገትን ፈጥሮ በዜጎች መካከል ፍትሀዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍልን አስከትሏል፡፡ በዚህ መልክ የቀጠለው ሸኩቻ ኮንትሮባንድ አስፋፍቶ ባህል እስከመሆን አድርሶታል። ዝርፊያውና ወንብድናውማ መደበኛ ተግባር ተደርጓል። በዚህ ምክንያት ሌብነት በዝቶ ድህነት ተስፋፍቷል። ድርጊቱ ተባብሶ በመቀጠሉ በዜጎች መካከል የኑሮ ልዩነት ፈጥሯል። ይህ አይነቱ ያልተገባ ሸኩቻ ግለሰቦችና ድርጅቶች ብልሹ አሰራሮችን ተጠቅመው ለራሳቸው ጥቅም ብቻ በማሰብ ያልተገባ ሀብት እንዲያከማቹ፣ በገበያው ጤናማ ውድድር እንዳይኖር እና የዋጋ ውድነት እንዲፈጠር የሚያካሂዱት አሻጥር ፍፃሜው ሀገርን ለከፋ አደጋ ህዝብን ለችግር የሚዳርግ መሆኑ ላይ ነው። ይህ በሕዝብና በሀገር ላይ የተወረወረው ክፉ በትር ሲውል ሲያድር የፖለቲካ ምህዳሩን በማዛባት ዴሞክራሲ እንዳያብብ እንቅፋት ከመሆን ባለፈ የህግ የበላይነት ጠፍቶ ህገወጥነትና ማናለብኝነት መንገሱ አይቀሬ ነው።

"ሳይቃጠ በቅጠል" እንደሚባለው ባልተገባ መንገድ በየትኛውም አካል የሚደረግ ሸኩቻዎችን ሳይራቡና ሳይባዙ ማስቆም ካልተቻለ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት መስፈኑ ፣ ጤናማ ውድድር መጥፋቱ ፣ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ ጠፍቶ እኔ ብቻ የሚለው ስርዓት መንሰራፋቱ አይቀርም። መንግሥት ያልተገቡ ሸኩቻዎች በአገራችን ላይ እያስከተሉት ያለውን አደጋና ሥጋት ከግምት አስገብቶ ዓላማቸውን ፣ አደረጃጀታቸውን ፣ አሁን ያሉበትን ሒደት እና እያደረሱት ያለውን ጥፋት በውል በመገምገም የማስተካከያ ዕርምጃ መወሰድ ያለበት ጊዜው አሁን ነው። ነገር ግን እያደገ የመጣውን ያልተገባ ሸኩቻ ማስቆምና መቆጣጠር ካልተቻለ በአሳሳቢ ሁኔታ የኀብረተሰቡን ጫንቃ እያጎበጠ እንደ ሸምጥ ፈረስ የሚጋልበውን የኑሮ ውድነት መግታትም ሆነ ሀገርን ወደፊት ማራመድ ከአቅም በላይ መሆኑ አይቀሬ ነው።

ስለሆነም አሁን ባለንበት ሁኔታ ችግሩ ስር የሰደደ እና የተባባሰ መሆኑን ተረድተን ህዝብን ለድህነት ሀገርን ለውድቀት ሳይዳርግ በመንግስት በተለይም ደግሞ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ኃላፊነት የተጣለባቸው ተቋማት ያልተገባ ጥቅም የማግኛ ሰንሰለቶችን እና ሸኩቻዎችን መልክ በማስያዝ መሬት የነካ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። እንደሕዝብም ቢሆን በመከላከል ፣ በማስቆም ፣ በመጠቆም ፣ ተባባሪ ባለመሆን እና ተሳታፊ ሆነው በተገኙ አካላት ላይም እርምጃ እንዲወሰድባቸው ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ስራዎች የሁሉንም እርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን ከወዲሁ ተረድተን ችግሩን ከስሩ መንቀል የዛሬ ስራችን ልናደርገው ይገባል ሰላም።